# ግልጽ ደብዳቤ ለኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት፤

## ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ

ይድረስ ለኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ሠራዊትና የፀጥታ ክፍል አባላት፤

__ጉዳዩ፡- የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ለባዕድ መሰጠትንና ዳር-ድንበር መደፈርን በተመለከተ፤__

ውድ አገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት አንድነቷንና ነፃነቷን በቀጣይነት ማስከበርና ማቆየት የቻለችው ተፈታታኝ ሁኔታና ተቀናቃኝ ጠላት ሳይኖራት ቀርቶ፣ ወይም በጎረቤቶቿ በጎ ፈቃድና አዘኔታ፣ ወይም የውጭ ደጋፊ ኃይል ኖሯት፣ ወይም እንዲሁ በታሪክ አጋጣሚ ሳይሆን ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገሩ አንድነትና ክብር ካለው ፍቅርና ቀናዒነት የተነሳ በከፈለው መራርና ክቡር መስዋዕትነት ነው።

የፖለቲካ ርዕዮቶቻቸውንም ይሁን ዕምነቶቻቸውን ተገን አድርገው የአገራችንን የውሃና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶቻችንን፣ ሲቻል በቀጥታ ለመቆጣጠር አለያም እንደልባቸው ለመቦጥቦጥ የፈለጉ የቅርብም ሆኑ የሩቅ ኃይሎች በተደጋጋሚ ያደረጉት ጥረት፣ ምኞት ብቻ ሳይሆን ቅዠት ሆኖ እንዲቀር የተደረገው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጎሣ፣ የሐይማኖት፣ የቋንቋም ይሁን የአካባቢ የልዩነት አጥር ሳያግደው፣ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች አንደ አንድ አገር ዜጋ በጋራ በመቆምና የሕይዎት መስዋዕትነት በመክፈል ነው። የተፈተለ ክር እንደሚጠነክር ሁሉ በዚኽ የአገራዊ አንድነት የጋራ ትግል ፈተና ሂደትም ሕዝባችን ትሥሥሩን የበለጠ እያጠናከረ እነሆ እስካሁን ሊለያዩት ለፈለጉ ሁሉ አልበጠስ ብሎ አስቸግሯቸዋል።

በአሁኑ ጊዜ የአገራችን አንድነትና ሉአላዊነት ላይ የተደቀነው ፈተና እስካሁን ከተለመደው በዓይነትም፣ በይዘትም፣ በአፈጻጸምም አንድ ቢመስልም፤ በጣም ልዩ፣ አስገራሚና የበለጠ አሳዛኝ የሚያደርገው ግን ይህ በአገር አንድነትና ሉአላዊነት ላይ የሚደረግ መሰሪያዊ ዘመቻ ተፈጻሚ እየሆነ ያለው ከውጭ በመጡ ኃይሎች ወይም በተወሰኑ ለጥቅም በተገዙ የውስጥ ተራ ተቀጣሪ ባንዳዎች ሳይሆን በማዕከላዊ መንግሥትነት ስም በሕዝብ ትከሻ ላይ በተቀመጠ ክፍል መሆኑ ነው። አዎን ይህ አዲስ ክስተት ገጽታውን ካሳየ ውሎ አድሯል። ይህ በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራ ወያኔ/ኢሕአዴግ የተባለ ቡድን የፖለቲካ ቅኝቱ የኢትዮጵያን አገራዊ አንድነት፣ ሉአላዊነትና ብሔራዊ ክብር በዋናነት መፃረር፣ ታሪኳን ማንቋሸሽና ሕዝቧን መናቅ ዓብይ ተግባሩ እንደሆነ በተደጋጋሚ በተግባር አረጋግጧል።

ማንኛውም በመንግሥት አካልነት የተሰየመ ክፍል ዋነኛና ተቀዳሚ ተግባሩ የአገርን አንድነትና ሉአላዊነት በቀናዒነት ማስከበርና የሕዝቡን ደኅንነት ማስጠበቅ ሲሆን፣ "አገር ሲያረጅ ጃርት ያፈራል፣ መሬት ሲያረጅ አራሙቻ ያበቅላል" እንዲሉ፣ ይህ የአቶ መለስ ቡድን ተግባር ግን ይኽንን መንግሥታዊ ኃላፊነት መወጣት አለመቻል ብቻ ሳይሆን ተፃርሮ የቆመ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በቁጭትና በሃዘኔታ የተገነዘበው ጉዳይ ነው። ለመሆኑ እንዴትና በምን ምክንያት ነው እንደዚህ ዓይነት ሤራ በራሱ ወገንና አገር ላይ የሚፈጽም ቡድን በማዕከላዊ መንግሥት ስም ለዚህን ያህል ጊዜ በዚህ ተግባሩ መቀጠል የቻለው?

በሁሉም ዘርፎች የተሰለፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት (እስከ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን መያዝ ድረስ አገሪቱ የነበራትን የባሕር ኃይል ጨምሮ) የእናት አገርን ዳር-ድንበር ከማስጠበቅ አልፎ ከአገሩ ውጭ ባደረጋቸው ተጋድሎዎችና በከፈላቸው ክቡር መስዋዕትነቶች ባስመዘገባቸው ስመ-ጥርና አኩሪ ተግባራት፣ አገሩንና ሕዝቡን ያኮራና በመልካም ስም ያስጠራ ክፍል ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሪዎቹ ለሚቀርብ አገራዊ ጥሪ ማቄን ጨርቄን ሳይልና ሳያመነታ አዎንታዊ ምላሽ በመስጠትና ሳይከፋፈል አንድ ላይ በመቆም፣ በትዕቢት ተሞልተውና በዕብሪት ተወጥረው በየጊዜው የአገራችንን አንድነትና ኀልውና ለመፈታተን ድንበር ገፍተውና ባሕር ተሻግረው የመጡ የኦቶማን ቱርክን፣ የግብጽን፣ የጣልያንን፣ የድርቡሽን፣ የሶማሌን፣ ወዘተ.. ዕብሪተኞች ድባቅ እየመታ ነው አገሩን ጠብቆ ያቆየው።

ኢትዮጵያ በገናናው የአክሱም ሥልጣኔ ጊዜ ለተበደሉና ለተጨቆኑ ዐረቦች ጦሯን ከባሕር ማዶ በመላክና አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ከመደምሰስ የማዳን ተልዕኮ ጀምሮ፣ በኮርያና በኮንጎ አኩሪ ዓለም-አቀፍ ሚናን የተጫዎተ ሠራዊት ባለቤት መሆኗ በኩራት የሚታወስ ነው።

እንኳን ከነነፍሱ የተማረከ ወታደር አንድም የወገን እሬሳ በጠላት እጅ እንዳይወድቅ አይከፍሉ መስዋዕትነት እየከፈለ ከፍተኛ የሙያ ብቃቱን ብቻ ሳይሆን ለወገኑ ያለውን የላቀ ፍቅር ያስመሰከረ ሠራዊት የነበራት አገራችን ኢትዮጵያ፣ በአሁኑ ጊዜ ንጹህ ዜጎቻችን አንድም ጊዜ ከኢትዮጵያ ሙሉ ባለቤትነትና ቁጥጥር ሥር ወጥቶ ከማያውቀውና ከትውልድ ትውልድ ከተላለፈላቸው አንጡራ መሬታቸው በሱዳን የባዕድ ጦር ታፍነው፣ በባዕድ አገር በእስር እንዲንገላቱ፣ ሃብታቸውና ንብረታቸው በነዚሁ ባዕዳን እንዲቃጠልና እንዲወረስ፣ መሬታቸውም ወደ ባዕድ እንዲከለልና እነሱንም ከነመሬታቸው አሳልፎ የተሰጠበት አሳፋሪና አሳዛኝ ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

አፄ ቴዎድሮስ ከጉልምስና እስከ ንጉሠ-ነገሥት የተዋደቁለት፣ አፄ ዮሐንስ ከፖለቲካ ሥልጣንና የግል ዝና ይልቅ ለአገራቸው አንድነትና ለወገናቸው ክብር ቅድሚያ በመስጠት ራሳቸውን መስዋዕት ያደረጉላት፣ እልፍ-አዕላፍ ዜጎች አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰውና ምትክ የሌለው ሕይዎታቸውን ገብረው በከበረ መስዋዕትነት ታፍሮና ተጠብቆ የቆየው ከሱዳን ጋር የሚዋሰነው የአገራችን ድንበር በተለመደው የባዕዳን እብሪት ሳይሆን በወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች መሰሪ እቅድ እንዲደፈር ተደርጓል፤ ሆን ተብሎም በገፀ-በረከትነት ለሱዳን ተላልፎ እየተሰጠ ይገኛል።

በአገራችን የመከላከያ ኃይሎች ውስጥ ከተራ ወታደር እስከ ከፍተኛ የአዛዥ ደረጃ ላይ የሚገኝ የሠራዊቱ አባል ሁሉ ምንጊዜም ሊረሳ የማይገባው፣ ይኸ ክፍል የተቋቋመውና የሚተዳደረው ጎስቋላው አርሶ-አደር ገበሬ፣ ሠራተኛው፣ ሌላውም የኅብረተሰብ ክፍል በድሃ ጎኑ ከአፉ ነጥቆ በሚከፍለው ግብር እንደሆነና ዓላማውና ተልዕኮውም የአገሩን ዳር-ድንበር ለማስከበርና ለወገኑ አለኝታና መከታ እንዲሆን እንጂ፣ አገሩን አሳልፎ ለመስጠት ወይም አገሩን አሳልፈው ከሚሰጡ ጎን እንዲሰለፍና ወገኑን እንዲወጋ አይደለም። የኢትዮጵያን አገራዊ አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስከበርና ለመጠበቅ “ከራስ በፊት ለአገር” ብሎ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሥር ቃለ-መኀላ የፈጸመ የማንኛውም የአገር መከላከያ ኃይሎች ክፍል አባል፣ የአገር አንድነትና የሉዓላዊነት አደጋ ከየትኛውም አቅጣጫ ይምጣ ከየት፣ አደጋውን የመመከትና ሤራውን የማክሸፍ ታሪካዊ፣ ሕጋዊና ሙያዊ ግዴታ አለበት።

የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ የመንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በሕዝባችንና በሠራዊታችን መስዋዕትነት ተከብሮ የኖረውን አንድነትና ሉዓላዊነት በቀጥታ የሚፃረሩና የሚጎዱ ተግባራትን ተፈጻሚ ለማድረግ ሲል ታሪክ የሻራቸው የባዕዳን ቅኝ ገዥዎችን ያረጁ ያፈጁ ውል ተብየዎች ከመቃብር እየቆፈረ በማውጣት ለሚወስዳቸው ፀረ-ኢትዮጵያ እርምጃዎች ዋቢ ማድረግን ሥራየ ብሎ ተያይዞታል። ይኸም አድራጎት ገና 'ሀ' ብሎ የመንግሥት ሥልጣን እንደያዘ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በሌሎች ዓለም-አቀፍ መድረኮች “የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ” እንዲሉ ነፃ እንወጣለን ከሚሉት የበለጠ ዋና ተሟጋችና ባለጉዳይ በመሆን ኤርትራ ከእናት አገሯ እንድትገነጠልና ሕዝባችን እንዲከፈል፣ አገራችንም ወደብ-አልባ እንድትሆን በማድረግ ነው የተጀመረው። በብዙ ድካም የተገነባውን የአገሪቱን የመከላከያ ኃይል በመበተንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ትጥቁን እንዲፈታ በመደረጉም፣ ሕዝባችን በራሱ መሣሪያ በሽዓብያ እንዲወጋ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የአገዛዙን በደል ወደጎን አድርጎ፣ ለአገሩ ፍቅርና ክብር ሲል፣ ከዳር-እስከ-ዳር ተንቀሳቅሶ፣ ጥቃቱ በቀጥታ ለተሰነዘረበት የትግራይና የአፋር ክልል ወገኑ በአፋጣኝ በመድረስ፣ የተቃጣበትን ድፍረት በተለመደ አትንኩኝ ባይ ባኅሪውና ቆራጥ እርምጃው፣ በብዙ አሥርተ-ሽዎች የሚቆጠሩ ልጆቹን ገብሮ ቅጽበታዊ ድልን ተቀዳጅቷል። ሆኖም፣ የአቶ መለስ ዜናዊ ቡድን የኢትዮጵያ ሕዝብና የአገሪቱ መከላከያ ሠራዊት የከፈሉትን መስዋዕትነት ዝንብ እንኳ እንደሞተበት ሳይቆጥር፣ በመራር መስዋዕትነት በጦር ሜዳ የተገኘው ድል የቀረችዋን ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ባስከበረ መልኩ እንዳይቋጭ በተለመደው የሕዝብ ንቀት መንፈስና ሆን ተብሎ በታሰበበት መልኩ መና እንዲቀር ሆኗል። አልፎም፣ የግፍ ግፍ እንዲሉ፣ ለመከላከል ተገድዳ ድል ባደረገችው ኢትዮጵያ መወሰን የሚኖርበት ሰላም፣ ጋፍኛ በድል ተመችዋ ሽዓብያ በ“ሰላም” እንድትረታ ያመቻቸውን “ውል” በራሱ አነሳሽነት አልጀርስ ላይ በመፈረም ወራዳ የክህደት ተግባር ፈጽሟል። ይኸ በመደረጉም በከፍተኛ መስዋዕትነት ድል ያደረገ ሠራዊታችን ደመ-ከልብ እንዲሆንና አገራችን ለቀጣይ አለመረጋጋት እንድትጋለጥ ሆኗል።

በአሁኑ ጊዜ የመለስ ዜናዊ ወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ታሪክን፣ ባህልንና ሕግን በተላለፈ መልኩና ከሕዝብ ጀርባ በተለመደው መሰሪያዊ የእብሪት ባኅሪ ከሁመራ እስከ ጋምቤላ ከ1600 ኪሎ ሜትር በላይ እርዝማኔና እስከ ስድሣ ኪሎ ሜትር ጠልቆ የሚገባ የኢትዮጵያን አንጡራ ለም መሬቶች ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት ዳግም በዋቢነት ለማቅረብ የሚሞክረው የጎረቤት አገር የሆነችው ሱዳንን በቅኝ ገዥነት ይገዛ የነበረው አገር የእንግሊዝ አንድ ሻለቃ ግዌን የሚባል ግለሰብ በኢትዮጵያ በኩል ተወካይ ሳይኖር ብቻውን እንደፈለገና ዋናው ንጥጥሩ ወደፊት የዓባይን ምንጭ ለመቆጣጠር ሁኔታን ያመቻቻል ብሎ ባሰበው መልክ በወረቀት ላይ ያሠፈረውንና ከአፄ ምኒልክ እስከ ደርግ የነበሩ የኢትዮጵያ መንግሥታት ይኽንን መሠረት በማድረግ በሱዳን በኩል ሁኔታው አመች ሆኖ በታያቸው ጊዜ የሚቀርብን ጥያቄ ተፈጻሚ ማድረግ ቀርቶ አንድም ጊዜ አስገዳጅነት እንዳለው ሕጋዊ ውልነት ያልተቀበሉትና እውቅና ያልሰጡትን ጉዳይ ከተቀበረበት ቆፍሮ በማውጣት ነው፡፡

ለመሆኑ አቶ መለስና ተባባሪዎቻቸው እነኝኽን የመሣሰሉ፣ የአገርንና የሕዝብን ጥቅም በቀጥታ የሚፃረሩ፣ አሳፋሪና አዋራጅ፣ ቀደም ሲል በነበሩ መንግሥታት በቀጥታ ውድቅ የሆኑና ተቀባይነት ያልነበራቸውን፣ ሞተው የተቀበሩና ሕጋዊነት የሌላቸውን፣ በታሪክም ተደጋፊነትና ተቀባይነት የማይኖራቸውን “ዋቢዎች” በተደጋጋሚ ሲያቀርብ አንድም ጊዜ በተመሣሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያን የወደብ ባለቤት ለማድረግም ይሁን አንድነቷ ይበልጥ እንዳይሸረሽር ለማድረግ ምን አደረገ? ለመሆኑስ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት፣ በአንድነቷና በሉዓላዊነቷ ላይ ይኽንን ያኽል አምርሮና ሥራዩ ብሎ መዝመቱስ ለምንድነው? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ማንኛውም የሠራዊት አባል ይሁን የፀጥታ ሠራተኛ ሁሉ፣ ማንን እያገለገለ እንዳለ፣ ታማኝነቱስ ለማን እንደሆነ - ለአገርና ለሕዝብ ወይስ የአገርን አንድነትና የሕዝብን ክብር ለሚጠናወት ግለሰብና ቡድን? ብሎ - መጠየቅና መልስ መስጠት ይኖርበታል፡፡

የሠራዊት አባላት ሆይ!

ተራ ዜጎች በራሳቸው ስንቅና ትጥቅ የወር ተረኛ በመሆን ዳር ድንበር ሲያስከብሩ ከነበረበት የድሮ ጊዜ ጀምሮ በአርቆ አስተዋዩ አፄ ቴዎድሮስ መደበኛ ሠራዊት ተቋቁሞ፣ በዘመናዊ አደረጃጀት ተዋቅሮ እስከ ደርግ ዘመን ድረስ የነበረው ሠራዊት ታማኝነቱ ለግለሰብና ለቡድን ሳይሆን ለአገር እንደነበር ይታወቃል፡፡ ታማኝነትን ለአገርና ለሕዝብ በማድረግ የሠራዊቱን መልካም ታሪክ ቀጣይነት በተግባር የማሳየት ወይም ነገ እንደ ጤዛ የሚረግፍና እንደ ጉም የሚተን ጊዚያዊ ጥቅምን በማስቀደም የአንድ ፓርቲና ግለሰብ የግል ተቀጣሪና አገልጋይ በመሆን የአገዛዙ ጭቆና መሣሪያ መሆንና በአገርና በሕዝብ ላይ ግፍና በደል እንዲደርስ በማስቻል በታሪክና በሕግ ፊት በግልም ሆነ በወል ተጠያቂ መሆን ምርጫው የእያንዳንዱ መለዮ ለባሽና የመከላከያና የፀጥታ ኃይሎች አባል ይሆናል፡፡

ባለፉት አሥራ-ስምንት የአቶ መለስ አገዛዝ ዓመታት የአገራችን አንድነት ተናግቶ፣ ወደብ-አልባ ሆነን፣ ከራስህ ጥቅም በላይ በቅንነትና በቆራጥነት ለማገልገል ቃለ-ሙኀላ ሰጥተህ የተሰለፍክላት አገርህ ከአንድ የውጥረት ሁኔታ ወደሌላ የባሰ የውጥረት ሁኔታ እየተሸጋገረች፣ አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን የበለጠ የሚፈታተኑ የውስጥ፣ የአካባቢና ዓለም-አቀፍ ጠላቶች እንዲበራከቱና እንዲጎለብቱ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱ ታፍኖ፣ ጥቂቶች በድሎት የሚንደላቀቁባት፣ ሰፊው ሕዝብ ታይቶ ተሰምቶ ለማያውቅ መረን የለቀቀ ችግር ተዳርጎ የጉስቁልና ኑሮ በሚገፉበት፣ ዜጎች በአመቻቸው መንገድ ሁሉ ከሚወዷት አገራቸው በገፍ እንዲሰደዱ፣ ብዙዎችም መዳረሻቸው ሳይታወቅ፣ በርካቶችም ለአሰቃቂ ሞት እየተዳረጉ፣ ወዘተ... ያለበት ጊዜ እንደሆነ አንተም ታውቃለህ፡፡

በጣም የሚያሳዝነው ግን የአቶ መለስ ዜናዊ ወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ የሕዝብን መብት ለማፈንም ይሁን፣ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም በሚያደርጋቸው የውክልና ጦርነቶች፣ የራሱን ወገን ከቤቱና ከቀየው ለማፈናቀልም ይሁን፣ የአገርን መሬት እንዳሻው ቆርሶ ለባዕዳን ለመስጠት፣ ወዘተ.. በመሣሪያነት የሚጠቀመው፣ ለግለሰቡ ወይም ለቡድኑ ሳይሆን የአገርህን አንድነትና የወገንህን ክብር ለማስጠበቅ ቃለ-ሙኀላ የፈጸምከውን አንተኑ መሆኑ ነው፡፡ መብት ቢገፈፍ፣ መሬት ቢወረስ፣ ወዘተ... የጊዜ ጉዳይ ነው ሊመለስ ይችላል፡፡ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ አሁን እየተደረገ ያለው ግን ወገኖችን እስከ መሬታቸው ለባዕድ አሳልፎ የመስጠትን ያኽል ከፍተኛ ጥፋት ብቻ ሳይሆን የመጨረሻ ከባድ የወንጀል ተግባር ነው፡፡

በወታደራዊ ሕግ እንደሚታወቀው ማንም ከጠላት የተባበረና ተግባሩ በመረጃ የተረጋገጠበት ሁሉ አድራጎቱ አገር-ክህደት ስለሆነ ቅጣቱ የማያወላዳና ግልጽ ነው። ይህ አገዛዝ አሁን በሱዳን አዋሳኛችን እየፈጸመ ያለው ዳግም የአገር-ክህደት ወንጀል ነው።

ስለሆነም ማንኛውም የሠራዊት አባል በዚህ ወገኖችን አስገድዶ ከመሬታቸው የማፈናቀል ተግባርና የሱዳን ባዕዳን በኢትዮጵያ ምድር እንዲሰፍሩ በውል ለማስረከብ በሚደረግ እርምጃ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተባባሪ የሆነ ሁሉ በአገር-ክህደት ሜራ ውስጥ እንደተሳተፈ እንደሚቆጠር ልብ ይሏል። በተለይም ከመስክ መኮንን ጀምሮ ያሉ አዛዦች ኃላፊነታቸው የከበደ፣ ተጠያቂነታቸው የላቀ እንደሆነ ሊያውቁትና አጥብቀው ሊያስቡበት ይገባል።

በእንደዚህ ዓይነት የአገር-ክህደት ወንጀልና ሰላማዊ ዜጎችን የመሸጥ ተግባር ላይ የተሳተፈ ሁሉ በተለመደ "ታዝዤ ነው፣ ትዕዛዝ ተቀባይ ነኝ፣ አለቆቸን ጠይቁ" የሚል ምክንያት ፈጽሞ ተቀባይነት አይኖረውም፣ ከተጠያቂነትም አያድንም። ትዕዛዝ ከማንም ይምጣ ከማን፣ ትዕዛዙ አገርንና ሕዝብን የሚጎዳ እስከሆነ ድረስ፣ በተለይም አሁን በመደረግ ላይ እንዳለው አገርን አሳልፎ የመስጠትን ያኽል ከባድ ወንጀል ውስጥ የሚያስገባ መሆኑ እየታወቀ ትዕዛዝን መቀበል ሕጋዊነትም ሆነ አግባብነት አይኖረውም። እኛ የድንበሩን ጉዳይ በቅርበትና በልዩ ትኩረት የምንከታተል ወገኖች ብቻ ሳንሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳዩን እየተከታተለና እነማን በዚህ ሜራ እንደሚሳተፉ ዝርዝር እየተያዘ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ስለዚህ በተለይ የሠራዊት አባላትና የፀጥታ ክፍል ሠራተኞች የሆናችሁ ዜጎች ሁሉ የመለስ አገዛዝ በሚያደርገው በዚህ እጅግ አሳፋሪ የአገር-ክህደት ተግባር ተባባሪ እንዳትሆኑና በሕግና በታሪክ ፊት ተጠያቂ በመሆን እናንተን ብቻ ሳይሆን የልጅ ልጆቻችሁን ከዝንታለም ሃፍረትና ፀፀት እንድታድኑ፤ እንዲሁም የአገሩን ዳር ድንበር ላለማስደፈርና የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጎትቶ ያመጣበትን ወራሪ የባዕድ ኃይል ከአገሩ ምድር ነቅሎ ለማስወጣት ሕዝቡ አቅሙ በፈቀደለት መንገድና በልዩ ልዩ መልክ የሚያደርገውን የሞት የሽረት ትግል እንድትደግፉ፤ ከጎኑም በመቆም ሙያዊና የዜግነት ግዴታችሁን እንድትወጡ ጥሪያችንን በአጽንዖት እናቀርባለን።

የአገራችን ዳር ድንበር አይደፈርም!
የኢትዮጵያ አንድነት በልጆቿ ኅብረት ይከበራል!!

**የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ**
**(Ethiopian Border Affairs Committee)**
**P.O.Box** 9536 *** Columbus, OH 43209, USA**
E-mail: ethiopianborder@yahoo.com

**ጥር ፳፯ ቀን ፪ ሺህ አንድ ዓ/ም**
(February 4, 2009)